# ☆ ዴሞክራሲያ ☆

************************
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *
************************

ልዩ ዕትም ግንቦት 1994 ዓ.ም.

## ኢሕአፓና የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ

የኢትዮጵያ ህልውና ራሱ ለአደጋ በተጋለጠበት፤ድንበሯ ለባዕዳን ፖለቲካዊ ውሳኔ ሰለባ እንዲሆን በተፈረደበትና የሀገርና የሕዝብን አንድነትና ህልውና ማረጋገጥና ማስከበር የትግሉ ተቀዳሚ ተግባር ሆኖ በሚገኝበት በዛሬው ወሳኝና ታሪካዊ ወቅት ኢሕአፓ የኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅና ለማስከበር ምን መደረግ አለበት ለሚለው ፈታኝ ጥያቄ የራሱን መልስ በመስጠት እምነቱን በማያዋላዳ መንገድ እንደገና ይገልፃል።

በተለመደው አቀራረብ የብሔር/ ብሔረሰብ ጥያቄ ተብሎ የሚጠቀሰው የሕዝብን እኩልነትና መብት የሚመለከተው ቢ,ይ ችግር የተከሰተው አንዳንዶች እንደሚሉት በግራ ክንፍ ርዕዮት ያመነው ተራማጁ ምሁር ወይም የተማሪው እንቅስቃሴ ከአፈር አድበልብሎ ወይንም ከአየር ቆንጥሮ እነሆ ጥያቄ ተገኘ ወይንም ተፈጠረ ብሎ ስላመጣው አልነበረም። በወቅቱ የነበረው የአፄው ሥርዓት በሕዝብ መህል በመደብ፤ በሃይማኖትና በፆታ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በውልደትም–ኋላ ብሄረሰብ በተባለውም የተነሳ– በግልፅ ልዩነት ያደርግ ነበር።በቋንቋውና በማንነቱ ደረጃ የሙሉ ዜግነት ስሜት እንዳይኖረው የተደረገው ሕዝብ ቁጥር ቀላል አልነበረም። ይህ የብሔረሰብ ጭቆና ሊባል የበቃው ሁኔታም በተለይ በደቡቡ ክፍል ከጪሰኝነት ማለትም ከመሬት ባለቤትነት መነፈግና ከምርትም ውስጥ በርከት ያለውን ክፍል ከመገበር ጋር የተያየዘ ስለነበረ ጥያቄው በቀላሉ የማይታለፍ ነበር። ያም ሆኖ ደግሞ የፊውዳሉን ስርዓት ይታገሉ የነበሩት ወጣቶች ለጉዳዩ የሌለውን ክብደትና የማይገባውን ትኩረት በመስጠት ቅድሚያን አልሰጡትም። የኢትዮጵያ ተማሪ እንቅስቃሴ ሕዝባዊ ትግሉን የጀመረውና ያስተዋወቀው "በመሬት ለአራሹ" መፈክር ሲሆን ይህ የተማሪው ትግል እየተፋፋመ በሚሄድበትም ወቅት የኤርትራ እንቅሰቃሴ (በጀብሀ አማካይነት)፣ በባሌ በእነዋቆ ጎቱ የሚመራውና ኋላም በሶማሊያ የተደገፈው የትጥቅ ትግል፣ የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ ወዘተ... በመድረኩ ነበሩ። የብሔረሰብ ጥያቄ ሊባል የበቃው ጉዳይ መፍትሄ ይሰጠኝ ብሎም ይጠይቅ ነበር ማለት ይቻላል። ተራማጆቹ ያለን ችግር አይተውና አለ ብለው መድኃኒት በመፈለጉ ተግባር ላይ አተኮሩ እንጂ ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ላይ አልተሰማሩም።

ሕዝብን በስፋት አስተባብሮ በጋራ ጠላት ማለትም በሥርዓቱ ላይ ለማስነሳት በነበረው ጥረት በግድ ለጥያቄው ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። ይታገሉ ከነበሩት ተራማጆች ውስጥ የተወሰኑቱ ችግሩ የአካባቢ ወይም የአውራጃዊነት ችግር እንጂ ሌላ አይደለም ሲሉ ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የየራሳቸውን ቋንቋ የሚናገሩና በሚሊዮን የሚቆጠሩ (ስለዚህም ጎሳ መባል የማይገባቸው) ስላሉ እነሱን ብሔረሰብ ጥያቄውም የብሔር/ብሔርሰብ ጥያቄመባሉ ተገቢ ነው የሚል አቋም ያዙ። በወቅቱ ጠንካራ የነበረው ተራማጁ ክፍል ደግሞ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዩተዓለም የሚያምን ስለነበረ የሕዝብን አንድነት ለማስረገጥ አመቺ

ሁኔታና አመኔታን ለመፍጠር ደግሞ የብሔረሰቦችን የራስን ዕድል የመወሰን--ማለትም እስከመገንጠል ድረስ- መቀበል አለበት የሚለውን አቅዋም አስተጋባ። ወጣቱ ያኔ ይህ የቲዎሪ አቅዋም በገቢር ሊኖረው የሚችለውን አንደምታና ለጠባብ ብሔርተኞችም ምንኛ ሊያመች እንደሚችል በበቂ ግንዛቤ አልነበረውም ቢባል ስህተት አይሆንም። የግራ ርዕዮት ተከታይ የነበረው የወጣቱ ክፍል ጭቁኑ ሕዝብ አንድ ነው፤ በጋራ የመደብ ጭቆናን ካስወገደ በዴሞክራሲ መብቱ ተከብሮ በአንድነት ይኖራል፤ የመገንጠልንም አማራጭ አይወስድም የሚል ያልተፈተነና ያልተረጋጋጠ እምነት ነበር የሚከተለው። በጠባብ ብሔረተኛነት አስተሳሰብ የተቀየደው የጭቁን ብሔረ ሰቦች ክፍል- በተለይ- ሊያመጣ የሚችለው መዘዝ በጊዜና በሚገባ አልታየም ነበር። ኢሕአፓም ከተመሰረተ ጀምሮ የዚሁ የተሳሳተ ግምትና አቅዋም አንፀባራቂ ሆኖ ለረጅም ጊዜም መቆየቱን ተመክሮውን በመረመረ ጊዜ ያመነውና ከዚያም ለማስተካከል የጣረው ነው። በአንፃሩ ግን ከግራው ርዕዮት ርቂያለሁ ግን አንድነትና ለውጥን እመኛለሁ ያለው የኅብረተ ሰባችን ክፍል- በቁጥር የማይናቅ ክፍል- ለዚህ መሠረታዊ ችግር ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ለማቅረብ አለመጣሩ ብቻ ሳይሆን ችግሩ መኖሩንም ሳይረዳ ቆየቷል።

በወቅቱ ገጥጦና አፍጦ ይታይ የነበረው ትምክህትንም የሚያንጸባርቅ ጭቆና ስለነበረም ይህንኑ በማውገዝና በመታገል ላይ ትኩረት በመስጠቱ ጠባብ ብሔረተኞች አመቺ ሁኔታ ተፈጠረላቸው። የደርግ መንግስትም እንደ ኢሕአፓ ዓይነቶቹን ኅብረ ብሔራዊ ድርጅቶች በሽብር ባጠቃ ጊዜ ጠባቦች ለመጠናከር ሌላ ዕድልን አገኙ። ይህ ቢባልም በዚያን ዘመን ሕዝቡ ላይ ይደርስ የነበረው በደልና የእኩልነት መጥፋት ዛሬ ዓመታት ስላለፉና የተሻለ ስላልመጣ ሊካድ የሚችል ጉዳይ አይደለም። የነበረውን የጭቆና አይነትና መጠን በውል መረዳት እንጂ መካዱ ተገቢ አይመስለንም። ጭቆና ነበር ወይም አለ ስለተባለ የሌላው ወገን ሕዝብ በሙሉ የገድ ጨቋኝ ነበር ወይም ነው ብለው ገዢውን ማለትም ተጠያቂውን ክፍልና ሕዝብን በመደባለቅ አንዱን የሕዝባችን ክፍል በጅምላ በጨቋኝነትና ብሎም በጠላትነት መመደብ ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው። እንደ ወያኔ ካሉት÷ እያንዳንዱ አማራ ከጭቆናው ትርፍራፊ --ተረፍ መረፍ-- እያገኘ ስለሆነ ጨቋኝ ነው ይሉ ከነበሩት÷ ከዚያም አልፈው በጠላትም ከፈረጁት ጋር ደግሞ ኢሕአፓ ያልተቋረጠ ትግል ያካሄደ መሆኑ የሚታወቅና ሊታበልም የማይችል ነው። ይህ ከወያኔና መሰሎቹ ጋር የተደረገው ትግል ግን በሀገራችን ውስጥ የነበረውን የመብት ረገጣ በመካድ አልነበረም። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አማራ ተባለ ኦሮሞ፤ ትግሬ ተባለ ጉራጌ፤ ሶማሌ ተባለ ቤኒ ሻንጉል-ጉምዝ ወዘተ... በሥርዓቶቹ በአንድ ላይ እየተጨቆነ ቢሆንም በማንነቱ ደረጃ ደግሞ አንዱ ከሌላው ለየትና ላቅ ባለ ደረጃ መበደሉን ቢያንስ ራሱ የተበደለው ወገን ለእኩልነት ያሰማው በነበረው ጩኸት ሳይገልጠው አልቀረም ነበር። እየገለጠው እንደነበርም ያዳመጡት ክፍሎች ነበሩ። የነበረውን ሐቅ እንሸፋፍነው ካልተባለ በዚያን ጊዜዋ ኢትዮጵያ ውስጥም እኩልነት አልነበረም፤ ልዩነት ነበረ ፤ ሥርዓቱ ያዳላ ነበር። የትላንት ኢትዮጵያን የእኩልነት መዲና አድርጎ ለማቅረብ መነሳቱ በዚያውም "ተራማጅ ምሁራን የሌለ ችግር ፈጥረው ሀገር በጠበጡ" ብሎ ለማውገዝ መቃጣቱ ጭራሽ የተሳሳተ ይሆናል። ለዛሬውና ለነገውም የሕዝባችን የጋራ ትግል አይጠቅምም እንላለን።

በየካቲት አብዮት ጊዜ ተራማጁ ክፍልና ሕዝብም በአጠቃላይ አንድነትን በእኩልነትና በዴሞክራሲያዊ ግንኙነት ላይ ሊገነባ ጥረት አድርጎ ፤ ውጤቱም ጥሩ አቅጣጫ መያዝ- አበረታች እድገትም ማሳየት ጀምሮ ነበር። በአዲስ አበባ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ያደረጉት ሰልፍ ያነሳው የመብት ጥያቄ መወገድ ያለበትን ጉድለት ሲጠቁም የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንም በዚሁ ሰልፍ ላይ በድጋፍ ሰጪነት አብረው መሰለፋቸው ደግሞ የሀገሪቷን ብሩህ የወደፊት አማራጭ--መሆን ያለበትንና የሚያዋጣውን--የሚጠቁም አበረታች ተግባር ነበር። በወቅቱ ብቅ ያሉትና ተደማጭነትም እያገኙ የመጡት ሕብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ነበሩ። ይህ ብሩህ ተስፋ ግን በአምባገነን መኮንኖች በአጭር ተቀጨ።

ኢሕአፓና በአቅዋም የተለዩትም ሌሎች የወቅቱ ዋና ዋና የፖለቲካ ቡድኖች ቢሆኑም መሰረታቸው ብሔረሰብ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት እንደነበርና ኅብረ ብሔራዊው ትግልም ጎልቶና ገኖ ይታይ እንደነበረ በትግሉ እየተሳተፍን የነበርነው ብቻ ሳንሆን ሁኔታው ያስተዋሉት ሁሉ የሚያውቁት ነው፡፡ ልዩነቱ የፖለቲካ አቅዋሞችንና ፖሊሲዎችን በማማረጥ፥ በመደገፍና ባለመደገፍ ወይንም በመቃወም ላይ የተመሰረቱ ነበሩ እንጂ በደም ምርመራና የትና ከእነማን ተወለድክ በሚል ጥያቀና ምላሽ ላይ የተመሰረቱ አልነበሩም፡፡ የኅብረ ብሔራዊው ወይም ኢትዮጵያዊው ጎራ የነበረውን ቀና የአንድነት መንፈስና ለዚህም ጥሩ መሠረት ለመጣል ያስችላል ብሎ ያቀረበውንም መፍትሄ ጠባቦች በፅንፉ ብቻ አጉልተው "መገንጠል ወይም ሞት" የሚለውን መፈክር በማንሳት የራስን ዕድል በራስ መወሰን የተባለው የሥልጣን ማዕከላዊነትን በማስወገድና ሕዝብን የራስ አስተዳደርና ዴሞክራሲያዊ መብትን በማጎናፀፍ ደረጃም ተገባራዊ ሊሆን መቻሉ ተዘንግቶ መገንጠልን ማፅደቅ ብቻ እንደሆነ በጠባቦች ተተረጎመ ፡፡ (ወያኔ በመጀመሪያ ፕሮግራሙ ሁሉም ብሔረሰቦች ተገንጥለው የራሳቸውን ነፃ ሬፑብሊክ ያቋቁሙ፤ የትግራይ ነፃ ሬፑብሊክን እንመሰርታለን፤በጋራ እንታገል የሚሉ የአበይት ኢትዮጵያ አቀንቃኞችና ትምክህተኞች ናቸው ያለውን ያጤኗል) ፡፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን በግድ መገንጠልን ያዘለ አይደለም የሚለው የገባቸው የኤርትራ እንቅስቃሴዎች ደግሞ የኢትዮጵያ ቅኝ ተገዢ ነን የምንለውን ተቀበሉልንና እንደማንኛውም ቅኝ ግዛት በግድ ነፃ የመሆን መብታችን ይከበርልን አሉ፡፡ ኢትዮጵያን በጠላትነት በጥቅሉ በመፈረጃቸውም የጠባብ ብሔርተኞች ደጋፊና ፈጣሪም ሆነው በኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ላይ በጋራ ተነሱ፡፡ ኢሕአፓ የዚሁ ሴራ ዋነኛ ተጠቂ እንደነበር ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ታሪካዊ የሩቅና የቅርብ ጠላቶች ቅራኔዎችን በማባባስ የነበራቸው ሚና በቀላሉየሚገመት አልነበረም፡፡ የአባይን ወንዝ ያለገደብ መጠቀም የሞትና ሽረቷ ጥያቄ የሆነባት ግብፅ፤ በቀጥታም ሆነ ሱዳንን በመጠቀም፤ "ታላቋን ሶማሊያ" ለመፍጠር የምታልመዋ ሶማሊያ፤ ለተለያዩ ዓላማዎቻቸውና ግቦቻቸው መሳካት የኢትዮጵያን መዳከም ፈላጊ የሆኑት ምዕራባውያን ሀገሮች፤ በጠላትነት የፈረጇት በርካታ አረብ ሀገሮች ሁሉ ተገንጣይ ቡድኖችን ደግፈዋል፤ አበረታተዋል፥ ረድተዋል፡፡ ይህ የውጭ ኃይሎች ሚና እንዳለ ሆኖ ባዕዱ በነበረው የሀገራችን ውስጣዊ ችግር ተጠቀሙ እንጂ መብቱ ተከብሮለት በሰላምና በደስታ ይኖር የነበረውን ሕዝብ ቀስቅሰውና አታለው አላታገሉትም፡፡ ሥርዓቶቹ በደልና ግፍን ይፈጽሙ ስለነበርም ሕዝብን ለመከፋፈል ሥርዓቶቻቸው የነበራቸው ሚና ትልቅ ነበር ማለት ይቻላል፡፡የኤርትራን ችግር በሰላምና በጊዜ በመፍታት ደረጃ በአፄውም ሆነ በደርግ መንግሥቶች የተፈፀሙት ስህተቶች ለተከተለው ቀውስ ድልዳል መሆናቸው ደግሞ አያከራክርም፡፡ ሀገሪቱን ባጠቃላይ በተመለከተም ከኢትዮጵያ ሕዝብ በርካታውን በተለያየ ደረጃም ቢሆን የብሔር ጭቆናው የሚመለከተውን ክፍል የበደልና የበታችነት ሠለባ አድርጎ ኢፍትኃዊ በሆነ መንገድ መግዛት ያስከተለው መዘዝ የሚድበሰበስ አይደለም፡፡ ሐቁ ተበራይቶ መውጣቱ ከወደፊትዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የዚያን ዓይነት ሁኔታ እንዳይመለስ ለማድረግ ከተለያዩ ብሔረሰቦች በሚወለዱት ኢትዮጵያውያን መሐከልም ዘላቂ መተማመንን ለመፍጠር አስፈላጊ ነው እንላለን፡፡

በመሰረቱ ወያኔና መሰሎቹ የትምክህት ሌላኛው ገፅታ ናቸው፡፡ ጠባብ ብሔረተኛነት ትክክለኛ ግንዛቤ ሳይሆን ዝንፈት ነው፥ አልሚ ሳይሆን አጥፊም ነው፡፡ ሆኖም ግን ጠባብ ብሔረተኛ ቡድኖች እስትንፋስ ያገኙትና ሊኖሩም የቻሉት የሕዝብ እኩልነት ተረጋግጦ ሊገኝ ካለመቻሉ የተነሳና አነሰም በዛ የተወሰነ ድጋፍ ከሚመለከተው ብሔረሰብ ስላገኙም ነው፡፡ ስለዚህም ለችግሩ የመሠረት ድንጋይ ያኖሩት ሕዝብን እኩልነት የነፈጉት ሥርዓቶች መሆናቸውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የሀገሪቷን ሁኔታ ለማሻሻልና ለመለወጥ የታገሉት ኢትዮጵያውያን ይህንን አሉታዊ ቅርስ፤ ሁኔታና ችግር እንደሌለ ቆጥረው ሊታገሉ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ኢሕአፓን ብንወስድ ሁሉን ታጋይ ዜጋ በኢትዮጵያዊነቱ አቅፎ በጋራ ለዴሞክራሲያዊትና ሕዝብዋ በእኩልነት ለሚኖርባት ኢትዮጵያ ለማታገል የቆመና ለዚሁ ዓላማም የተዋደቀ ድርጅት ነው፡፡ የእነ ወያኔ ምርጫ ደግሞ ሌላና ሀገራችንን

የመገነጣጠል መንገድ ነበር:: ወያኔ ዛሬም በዚሁ ልክፍቱ እያጉዋራና እየተንዘፈዘፈም ሲቀጥል ሌሎች እሱው ባምሳሉ ያድቦለቦላቸው ቡድኖች ደግሞ ወያኔ በቀደደው ቦይ ገብተው እየፈሰሱ በኢትዮጵያዊነት ደረጃ ሳይሆን በብሔረሰብ መልክ መደራጀትን መርጠው እንዳሉ የምናየው ነው::

የትላንቱን የፖለቲካ ሁኔታ ለመገምገም ስንነሳ ከዚያ ሁሉ ውጣና ውረድ በኋላ ዛሬም ኢትዮጵያዊነትን በአደረጃጀት መልክም ማስቀደም ያልቻሉትን ማጤን ይኖርብናል። ወደ ቁም ነገሩ ስንመለስ ደግሞ ትላንት ሕዝቡ በእኩልነት የኖረበት ሥርዓት ነበረ ብለን ወደማይጠቅመን ንትርክ ከመግባት ይልቅ በወደፊትዋ ኢትዮጵያችን ውስጥ በሕዝቡ መሐከል መኖር ስለሚገባው በእኩልነትላይ የተመሠረተ ግንኙነትና አንድነት ትኩረት ሰጥተን መነጋገሩ ይጠቅመናል። በማንነቱ የተነሳ መብቴ ተገፈፈ ቢልም አሌ ብሎ ለመቃወም የሚያስችል በቂና አሳማኝ ሐቅ የለም። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ችግሩን ወደ ፅንፍ ገፍተው ሕዝብን በእርስ-በርስ ቅራኔ ወጥረውና በክለው መዓት ሊያወርዱ የሚሹትን መቃወምና በታሪክ ሂደት ሕዝቡ በክፉም በደጉም በአንድነት መኖሩንና የጋራ ሀገራዊ ታሪክና ቅርስም መካፈሉን ጫና ሰጥተን ማቅረብ ይኖርብናል። ሆኖም ግን ተበደልኩ ለሚል ሕዝብ፣ መብቴን ተነፈግሁ፣ እኩልነቴን ተካድኩ ለሚል ኢትዮጵያዊ ለምን ቁስልህ ተሰማህ- ለምንስ ስሜቱ ቆጠቆጠህ ማለቱ አግባብ ያለው ሊሆን አይችልም:: ዛሬ ደግሞ ከመቸውም ጊዜ በበለጠና በከፋ ደረጃ የብሔር ጭቆና እየተካሄያደ ነው ያለው ብንል ሐቅን ማቅረብ እንጂ ማጋነን አይሆንም። ተጨቁነናል፣ ከሌሎች ጭቁኖች ጋር አብረን በ "ጨቋኙ ሕዝብ" ላይ እንነሳለን ያሉት ጠባቦች ለሥልጣን ሲበቁ ራሳቸው ዛሬ ጨቋኝ ሆነው ብዙኀኑን እየበደሉና እንዲያውም አጥንትና ደም እየቆጠሩ በእነሱ "ሌሎች" የሚባሉትን እያሰቃዩ መሆናቸውንም እንታዘባለን።

በትግሉ ሂደት የሀገራችንን ታሪክና ተጨባጭ ሁኔታውንም በጥልቀት እያወቅን ስንመጣ በርዕዮታችን ቅኝት ይዘነው የነበረውን አቅዋም የት ላይ እንደተሳሰተ በመገንዘብ ችግሮችን ለመፍታት የተሻሉ አማራጮች ያልናቸውን ማቅረብ ጀመርን። ከወያኔ መሰል ጠባቦች ጋርም በነበረን የተጻራሪነትና የመራራ ትግል ግንኙነት ውስጥ የጠባብ ብሔርተኝነትን አደጋ በተጨባጭ በማየት በደፈናው የጭቁኖች የመብት ወይም የነፃነት ትግል ተራማጅ ይዘት አለው፣ ሊደገፍም ይገባል የሚለው አስተሳሰብ መታረም ያለበትና በሁኔታና ጊዜ ክልል ውስጥም መመዘን ያለበት አስተሳሰብ መሆኑን ለመገንዘብም ችለናል። እንታገለው የነበረው ደርግ በመሠረቱ በብዙ መልኩ ከወያኔም ከሌሎችም አምባገነኖች ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያየ ሲሆን በብሔር ሽፋን እንቅስቃሴ የጀመሩት የየአከባቢው ጠባቦች የራሳቸውን ጥቅምና አጀንዳ እንጂ የዴሞክራሲን መስፈን እንደማያስቀድሙ ለመገንዘብም በቅተናል። ጠባብ ብሔረተኞቹ ፍቅርን ሳይሆን ጥላቻና ክፍፍልን ማራገብ የዓለማቸው እምብርት መሆኑንም ማወቅ ችለናል። ወያኔ "ነጻ-አውጪ" ድርጅት ነኝ ብሎ ጫካ ይታገል በነበረበት ወቅት "ሕዝቤ" በሚለው በትግራይ ሕዝብ ላይ ሳይቀር የፈፀመውን ግፍ በሚገባም አይተናል። ከዚሁ ሁሉ ተመክሮአችን ግምገማና በዓለም አቀፍ ደረጃም የነበረውንና ያለውን እውነታ በማጤንና በመገንዘብ የጠባብ ብሔረተኝነትን አደጋ ይበለጥ አወቀነው በትኩረት ማጋለጥ ያዝ ። የኢትዮጵያን አንድነት እንፈልጋለን ከምንለው ውስጥ የተወሰኑት ክፍሎች፣ አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ማለታቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ በሀገራችን ውስጥ ያለን ሁኔታ በደፈናው ማለፉን ሲመርጡ እኛ ግን የነበሩትን ችግሮች አውጥቶ በመወያየት መፍትሂ መሻትን መረጥን።ችግሩን አድበስብሶ ማለፉ ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ግብ ላይ ግልጽነትንና መተማመንን ይቀንሳል። ተካፋይነትን በማጉደል ለአንድነቱ ጎራ ተጨባጭ አስተዋፅዖ ለማድረግ ከሚችሉት ውስጥ በብዛቱ የማይናቀውን ክፍል እንዳይሳተፍ ያደርጋል። ይህ የትላንት የማድበስበስ ሁኔታ ዛሬም ሲደገም እያየነው ያለ ስለሆነ በሚገባ ትኩረት ተሰጥቶት ሊመረመር የሚገባው ነው። በሀገር አንድነት ስም አንድነትን የሚሸረሽር ሁኔታ ሲከሰት ዝም ብሎ ከማለፍ መሠረታዊ የሆነውን የነበረ ችግር እያመኑ በጉዳዩ መነጋገርና መከራከርም ያስፈልጋል የምንለው ለዚሁ ነው። የአፄ ኃይለ ሥላሴም ሆነ የመንግስቱ ኃይለማርያም አገዛዞች የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በመርገጥ የፈፀሙዋቸው ተግባሮች በረጅሙ

ሲታዩ አንድነትን ጎዱ እንጂ አልጠቀሙም:: የደርግ መንግሥት ለእነ ወያኔና ሻዕቢያ መጠናከርና ለሕዝብም ወደ እነሱ ማዘንበል ያደረገውንም ያልታሰበበት አስተዋፅዖ አንረሳም:: በአንድ በኩል መንግሥት ሕዝብን የሚያስቆጡ ርምጃዎችን በመውሰዱ በሌላ በኩል ደግሞ ጠባብብሔረተኞች ፥ ጸረ አንድነት ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጠው በመነሳት ሁለቱም ወገኖች የራሳቸውን አጀንዳ ከግብ ለማድረስ መራወጣቸውን ቀጠሉ:: የዛሬው ከኮሶ የመረረ ከፋፋይና ሀገር-አጥፊ ወያኔያዊ ሥርዓት በፕሮግራምና እምነት ደረጃም ሀገርና ሕዝብን መከፋፈል ዓላማዬና ግቤ ነው ብሎ የተነሳና ለመገንጠል ዓላማም የታገለ ቡድን የተጋድሎው ፍሬ ነው:: በድንገት ዱብ ያለብን ዕዳ አይደለም:: የመገንጠልን መርዝ ሕገ መንግስቴ ባለው ወያኔያዊ ሰነድም (አንቀፅ 39) ውስጥ ያሰፈረ የለየለት ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል በመሆኑ እስከ ዛሬ ከነበሩት ቢያንስ በዓላማቸው ደረጃ ለሀገራዊ አንድነት ከቆሙት መንግሥቶች እጅግ በጣም የተለየ ነው:: ያለአንዳች መወላወል በጸረ-አንድነት ዕምነቱ የታወረ ቡድን ያመጣብን ጥንብርብር ሥርዓት ነው::

ለሕዝብ አንድነት በፅናትና በቆራጥነት ሳያወላውሉ መታገል ተገቢም ትክክልም ሆኖ እያለ አንድነት የፍላጎትና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርም ውጤት መሆኑን ከመገንዘብ ጋር የተያያዘ ሲሆን ደግሞ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል:: በጭፍጨፋና በመብት ረገጣ ላይ የሚገነባ አንድነት ረጅም ዕድሜ ላይኖረው ይችላል፥ ዕድሜው ቢረዝም እንኳዋን የሕዝቡ ውስጣዊ ሕይወት ጤናማነት ይጎድለዋል:: ስለዚህም መናወጥንና ግጭቶችን የሚያረግዙና የሚወልዱም ሁኔታዎች ይፈጠራሉ::

በታሪክ ሂደት ሀገሮች ሲገነቡ ወይም በተለምዶ አነጋገር "ሲቀኑ" ዴሞክራሲንና የሕዝብን ፍላጎት ተመሥርተው አይደለም:: በዓለም ውስጥ ዛሬ በሀገርነት እየታወቁ ያሉትን ስናይ ይህንኑ እንረዳለን:: የሀገር ግንባታው ሂደት በያለበት ጠመዝማዛና ሰላምን ሳይሆን ጦርነትን ያስቀደመም ነበር:: በሂደቱ የጠፋው ህይወት ቢያሳዝነንም የዘመኑ መሪዎች ዛሬ እንኳን ለእኛም አስቸግሮ ያለውን መቻቻልና ዴሞክራሲያዊነት ለምን ያኔ አላንፀባረቁም ብሎ መወንጀል ፍፁም ተገቢ አይሆንም:: ሕዝቦች በጦርነት አልፈው በጋራ መኖር ጀምረው መቶ ብቻ ሳይሆን ብዙ መቶዎችና ሺ ዓመታት ካለፈ በኋላ ግን የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ በመጎተት ቂምና ቁርሾን በማራገብ ከዘመናት በፊት ለፈሰሰ ደም የዛሬውን ትውልድ ተጠያቂ በማድረግ ክፍፍልን መቀስቀስና ማንገሱ የሚደገፍ ሳይሆን የሚወገዝ ነው::የነገ ኢትዮጵያን ዕድል ልንወስን ስንነሳም ሞተው ዘመን ያስቆጠሩ የዘመናቸው ነፀብራቅ የሆኑትን አፄዎች በዛሬ መነፅር በመመርመርና በማውገዝ ስንት መከራን በጋራ ያሳለፈን አንድነትና ኢትዮጵያዊነት መሰረዝ ፍፁም የሚቻልና የሚገባም አይደለም:: ያለፈው አልፎ በአንድ ሀገራዊ ክልል ሕዝብ በጋራ ለዘመናት ኖሮ በጋራ ደረጃም ማንነቱ ሲገለፅ ከኖረ በኋላ፥ ዛሬ በሕዝቡ መሐከል ልዩነት ኖረ አልኖረ ያንን መሠረታዊና ቀዳሚ ማንነቱን መካድ ጭራሽ አይቻልም:: የኦሮሞው፣ የወለይታው የጉምዙ፣የሀዲያው፣ የአማራው፣ የትግሬው ወዘተ... ሕዝብ የኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ባለቤት ነው እንጂ ኢትዮጵያዊነቱን ለማስረገጥ ድርድርን አይፈልግም:: ይህንን የሚክዱ ናቸው በሕዝብ አንድነት ላይ መርዝ የሚረጩት ማለትም ይቻላል:: በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ገደብ ሊጥሉብን ግድፈት ሊፈጠሩብን ሊያውገረግሩብንና ማንነታችንንም ሊክዱ የተነሱትን ሥርዓቶች የምንታገላቸውም ከዚሁ በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ካለን ጠንካራ ዕምነት የተነሳ ነው:: ኢትዮጵያዊነታችንን ሲክዱ አዎን ብለን መቀበል ሆነ መገንጠልን ማቀንቀን ደግሞ ስህተት መሆኑም ሊታመንበት ይገባል:: በመሆኑም ኢሕአፓ ለመብታቸው ከሚታገሉት ጎን እየቆመና እየታገለም ኢትዮጵያዊነትን በመካድ ለሚቃኝ የትግል ምርጫ ወይም ፕሮግራም ግን ተቃውሞውን ያሰማል እንጂ ድጋፉን አይሰጥም:: ጭቆና ስለተባለም ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ይዘቱና ሚዛኑም ሳይጋነን መታወቁ የግድ ነው እንላለን:: የወያኔን በሬ ወለደ ዓይነት የታሪክና የሐቅ ክለሳ ስንመለከት በጉዳዩ ላይ ይበልጥ ጥንቃቄ እንድናደርግ ሊጋብዘን ይገባል:: ማን ይበልጥ ተጨቆነ ማንስ ከዚያ ባነሰ ደረጃ ተበደለ በሚለው አጓጉል ክርክር ባንገባም አንዳንድ ጉዳዮችን መጠቆም ግን እንወዳለን:: ቢያንስ ትግራይ ለምሳሌ በጨሰኛ ስርዓት አለመበደሉን፣ አድልዎ ተደረገ ከተባለም በአንዳንድ መስኮች ሁኔታው ወያኔ ጨቋኝ

የሚለው ሕዝብ ራሱ ከሚኖርበት ሁኔታ ያልተናነሰ እንደነበረም መጥቀስ እንችላለን፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በነበሩት መንግሥቶች የልማትና ዕድገት ፖሊሲዎች ደረጃ የተረሱና ስለሆነም ኢትዮጵያዊነታቸው በጥያቄ ገብቶ የቆዩ ሕዝቦች--አንዳንዶቹ በደርግ ጊዜ ወደ ፖለቲካው ዓለም የተሳቡ- እንደነበሩም እናያለን፡፡

የተወሳሰበውን አስቸጋሪ ጥያቄ በጥሞና መርምረን ተገቢውን መፍትሔ ለመስጠት እንዳንችል ጋሬጣ የሆኑት ሥርዓቶች እንዳሉ ሆነው በፅንፍ ያሉት አጀንዳዎችና ስሜቶችም ያደረጉት አስተዋፅዖ በትኩረት መታየት ያለበት ነው፡፡ በአንድነት ፍፁምነት መፈክር ስም ወደ ጎጂ ፅንፍ በመጓዝ ብሶቶች የፈጠሩዋቸውን ልዩነቶችም ያለማድመጥ እንደነበረና እንዳለም ሁሉ በብሔረሰብ መብት ሽፋን ደግሞ ክልል መሥርተው አትድረስቡን-አትተቹን ተዉን በጥበት እንሸምጥጥ፤ ሕዝብን እናጋጭ፤ እንከፋፍል ያሉና የሚሉም ጎጂ ክፍሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ በብሔረሰብ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ተደራጁ፤ አንከፋፈል፤ ለወያኔ አንመቻች ብለን ለመምከር ለመተቸት ስንነሳ የብሔረሰብ መብታችንን ደፈራችሁ፤ ትምክህት አንፀባረቃችሁ ብለው አፋችን ሊለጉሙን ይጥራሉ፡፡ አሮጌ መጥረጊያ ቤት አያጠራምና ያለፈውን ሥርዓት ለመመለስ መባዘኑን ትተን ሕዝብ በእኩልነት የሚኖርበትን መንገድ እንፈልግ ስንል ደግሞ ስለ በደልና ጭቆና ማውሳቱ ወይም መኖሩን ማመኑ ራሱ ሕዝብን መከፋፈልና አንድነቱን መሰረዝ ነው ብለው በስህተት ደምድመው ባልገባቸው ያወግዙናል፡፡ ለእኛ መነሻችን የሕዝብን አንድነት ማጠናከር በመሆኑ ትምክህት ሆነ ጠባብነትን ማስተናገዱ ሀገርን ምንኛ እንደሚጎዳ እናውቃለንና የምንቃወማቸው ዝንባሌዎች ናቸው፡፡ በመጠሪያ ደረጃም ብዙ ሚሊዮን የሆነን አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ጎሳ ብሎ መሰየሙ ትክክል ባለመሆኑና ከተገቢው ስያሜ አንፃር ደግሞ ብሔር-በሔረሰብ ማለቱ ይሻላል ያልነውን ደግሞ በመለጠጥ ይህ መጠሪያ የተሰጠው ሁሉ የመገንጠል መብት ባለቤት መሆን አለበት ያልን አስመስለው ለማቅረብ የጣሩም ነበሩ፡፡ አያሌ ብሔረሰቦች ያሉባትና ከዚህም የተነሳ የደመቀችና ያማረባት ዴሞክራሲያዊት አንዲት ሀገር ልትኖረን-ልትገነባ ትችላለች ብሎ በማመን ኢሕአፓ ለዚሁም ታግሏል፡፡ ብሔረሰቦች አሉ ስለተባለ ሕዝብ አንድነቱን አጣ ማለት እንዳልሆነ ሁሉ አንድ ሕዝብ ስለተባለና ስለተደጋጋመ ደግሞ እውነትም አንድ ሆኗል ወይም የአንድነት መንፈስ ሰርፆበታል ማለትም አይቻልም፡፡ ስለዚህም ተገቢውን ስያሜ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ቃል ለሚሰይሙልንየቋንቋ ሊቃውንት ትተን በመሠረቱ የቋንቋና ሌሎችም ልዩነቶቻችን ለአንድነታችን መለሰተኛ መሆናቸውን መቀበልና በአግባብም መያዝ ይኖርብናል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢበደልም፤ ለእኩልነት ያደረገው ረጅም ትግል ከግቡ ባይደርስለትም በሀገሪቷ ረጅም ታሪክ በጋራ ኖሮ፤ ተጋብቶ ተዋልዶ፤ኢትዮጵያዊነቱን በጋራ አረጋግጦ በዚህ መልክ ሀገራዊ-ስሜትንም በጋራ እንደያዘ መካድ አይቻልም፡፡ ሕዝቡ ኢትዮጵያዊነታችን በማንም አይካድ ሲል ተደመጠ እንጂ ባዕድ ነን፤ ቅኝ ተገዢ ነን፤ ኢትዮጵያዊነታችንንምአደራድሩን ሲል ከቶም አልተሰማም፡፡ በደሙ ራሱ የፃፈውን የአንድነት ታሪክ ሊሰርዝ ሊከልስ ሲጥርም አልታየም፡፡ ልዩነቱ እንጂ አንድነቱ፤ በደሉ እንጂ ደስታው፤ የሚያፈራቅቀውና የሚያቀርነው እንጂ የሚያስተባብረውና ያፋቀረው ከቶ የማይታያቸው ክፍሎች--በተለይም ሌላ የሚጠበቅባቸው ከሕዝቡ አብራክ የወጡ ምሁሮች-በድፍረት ሊክዱት የሚከጅሉት የኢትዮጵያ ታሪክና ኢትዮጵያዊነት ራሳቸው የሚያረጋግጡት እውነታ ግን ሀገርም ታሪክም ሕዝብም የነበሩ፤ ያሉና ወደፊትም በአንድ የሚኖሩ መሆናቸውን ነው፡፡ በዚህ እውነታ ላይ ተመስርቶ ትምክህትና ጥበትን አስወግዶ የሕዝብን አንድነት በዴሞክራሲና እኩልነት ላይ ተክሎና አጠናክሮ የሀገርን አንድነት ማስከበር ሲገባ በተፃራሪው ፀረ አንድነት ጎዳናን መርጠው በዚህም በዚያም ሀገርንና ሕዝብን ለመከፋፈል የሚጥሩ ክፍሎች ዘወትር በታሪክ የሚወገዙ ይሆናሉ፡፡ የሀገር አንድነት ጉዳይ ጭራሽ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ሀገር እንደ ተራ ኩባንያ አልጠቀመም ወይንም አላተረፈም አክስሯል ተብሎ የሚዘጋና የሚፈርስ አይደለም፡፡ የአንድነትን ጉዳይ በአግባብና በጥንቃቄ አለመያዝ መዘዙ አስከፊ እንደሚሆን ሶማሊያን ዩጎዝላቪያን ከዚያም አልፎ የቀድሞይትዋን ሶቭየት ኅብረት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በቀላሉ ታይቶ የሚቆመርበት ወይም

የወያኔ የባዕድ ደጋፊዎች እንደሚሉን "ሙከራ" የሚደረግበት አይደለም:: የብዙ ኢትዮጵያዊ ደም የፈሰሰበት የሀገር አንድነት ጥያቄ የህልውና ጉዳይ ነው--ሌሎች ተልዕኮዎችና ህልሞች-ዕቅዶች ሁሉ በእሱ ላይ የሚመሠረቱ ናቸውና በቀላሉ ሊታይ የማይታሰብ ነው::

ኢሕአፓ ከተመሠረተ ጀምሮ ባመነበት መንገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና የመብት ባለቤትነት የታገለና ዛሬም የሚታገል ድርጅት ነው:: ነጋ ጠባ ጠላቶቹ አንዴም በትምክህትአንዴም በአስገንጣይነት ቢከሱትም ድርጅቱ የሀገርን ጥቅምና አንድነት አሳልፎ በመስጠትና በእምነቱም ላይ በመደራደር ታሪኩን አላቆሸሸም:: ከተመሠረተ በኋላ ለምሳሌ ከሻዕቢያ ጋር የነበረው ግንኙነት ኢሕአፓ የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት ከመቀበሉ ጋር ተጣምሮ መቅረብ ሲጀምር ኢሕአፓ እንደ ወያኔ በርከክ ብሎና ገብሮ የተባለውን የተቀበለና ታሪክን የካደ እምነቱን የለወጠ ሳይሆን በዚሁ የተነሳ ግንኙነቱን ያቋረጠ ድርጅት ነበር:: ዚያድ ባሬም ሆነ የአረብ ሀገሮች ለኢሕአፓ ሊያደርጉት የሚችሉት ድጋፍና ትብብር የኢትዮጵያን ህልውናን መካድን ወይም መፃረርን የግድ ባለ ጊዜ ኢሕአፓ "አላረገውም!" አለ አንጂ ለመሣሪያና ለገንዘብ ርዳታ ሲል መርሆውንና-ሀገሩን አልሸጠም:: የሀሰት ሊቀ መኳሶች ቢቀባጥሩም "ቪቫ ዚያድ ባሬ" ብሎም አልጮኸም፣ ሱዳን ድልድይ አፍርስ ሲለው እንደ ወያኔ እሺ ብለትዕዛዝ አለተቀበለም "እምቢ አላፈረሰም " አ ለ እንጂ፣ በስደት ወደ ሀገራችን ይመጡ የነበሩ የደቡብ ሱዳን ተወላጆችን ይዞ ለገዳይ አልመለሰም፣ በናቅፋ በረሀ ለጋና ወጣት ህይወትን እንደ ወያኔ ለጠመንጃ አልለወጠም:: ያኔ ይከተለው በነበረው ርዕዮት መሠረትና ለሰው ልጅ መብትም ከመቆርቆሩ የተነሳ፥ እንዲሁም ለመተማመንና ለጋራ ትግል መንገድ ይጠርጋል ብሎ በማሰብ የመገንጠልን መብት ቢያውቅም ይህ መብት እውን መሆኑ ሕዝብን ይጎዳል በማለቱና ለሕዝብ አንድነት በመሚገቱ ገና ከመጀመሪያው የብሔር ቅራኔ ቢይ ቅራኔ ነው፣መገንጠልም አማራጭ የለሽ መፍትሔ ነው ካሉት ከእነ ወያኔ ጋር ተቃርኗል፣ በፖለቲካና በጠመንጃም ተፋልሟል:: ወያኔ ያዝረበረበው ዓይነት የጠባብ ብሔረኝነት መርዝ ለሀገር ምንኛ ጠንቅ ሊሆን እንደሚችል ብዙኃኑ ገና ሳይገነዘቡት ኢሕአፓ ወያኔን በጠባብ ብሔረተኛት ፈርጆ በተቻለው ሁሉ ታግሏል:: የኤርትራ እንቅስቃሴዎችም ከከረረ ብሔርተኝነት እንዲላቀቁ የዚህኑ ተግባር አስፈላጊነት ካመኑት ጋር በመሆን በይፋም በሌላም መንገድ የአቅሙን ታግሏል:: በዚህ ትግል ኢሕአፓ ያደረገውን አስተዋፅዖ ወደፊት በአመቺ የታሪክ ሁኔታ መዘርዘሩ የሚቻል ሲሆን ድርጅቱ ይህንን መብት ሲቀበል መብቱ በስራ ይዋል በሚል ግትርና ጎጂም ይሆናል ካለው መንፈስ ሳይሆን መብት ማወቁ ለመተማመን ጥርጊያ ሆኖ ግና የሕዝብ አንድነት ጠቀሜታና አማራጭ የለሽነቱ ተቀባይነት ይኖረዋል በሚል ነበር::

በቲዎሪና በቃላት ሳይወሰን ኢሕአፓ ለችግሮቹ በተጨባጭ መፍትሄዎችንም ጠቁሞ እንደነበር ማስታወስም ይገባል:: የሀገር አንድነት ከግዛታዊ ክልል ባሻገር ከሕዝብ ጥቅምናአንድነት ጋር ተዋኸዶ እንዲገለፅና የጠባቦች የጥላቻ መሳሪያም እንዲሰበር ባለማቋረጥ ታግሏል:: የአንዱ ባህል፣ ሃይማኖት-እምነትና ቋንቋ ከተናቀና "ንፁህ ኢትዮጵያዊ" የሚል ሌላውን አግላይ ፈሊጥ ከገነነ፣ የዜጎች ዜግነት በጥርጣሬ ከገባና ንቀትና ጥላቻ ከተስፋፋ የሀገር አንድነትን ማረጋገጥ ያዳግታል ሲል ሳይታክትም አሳስቧል:: ወያኔያዊነት ለምሳሌ ከኢትዮጵያዊነት በመሠረቱና በመላ ይዘቱና ሂደቱም የተቃረነ ነውና ወያኔን ለመቃወም በወያኔ መንገድ መጓዝ ኢትዮጵያን እንደሚጎዳም ገና ወያኔ ለቤተ መንግሥት ሳይበቃ ጀምያብራራውና ያስጠነቀቀበትም ጉዳይ ነበር:: ይህንኑም እንደገና በማንሳት በጥር 1988 ዓ.ም " የሀገር የሕዝብ አንድነት- በምን መሰረት?" በሚለው ፅሁፉ ውስጥ የሚከተለውን አስፍሮ ነበር፣

"ለሀገር አንድነት የሚደረገው ታሪካዊ ገድል ከብሔረተኛነት ጋር መፋጠጡ የማይቀር ነው:: ብሔረተኛነት የበላይነትን በያዘበት ሁኔታና ተጨቋኛላሁ ብሎ በሚነጉድበት ወቅት የሕዝብን ብሶት ወስዶ በማጋነን ይስተጋባል እንጂ ምንም ጊዜ ቢሆን የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት መሠረት አድርጎ አይነሳም:: ብሔረተኛነት ሆነ የመገንጠል ጥያቄ የሕዝብ

አይደሉም፡፡ የገዢው መደብ ወይም ገዢ ለመሆን በሚከጅለው ክፍል የሚነገብ ርዕዮት በመሆኑ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ "የብሔረሰቡን" ሰፊ ሕዝብ ጠላት ከሚለው ሕዝብ ጋር ማፋራቀቅ፣ማጣላት፣ ማዳማትና ማለያየት ዋነኛ ተልዕኮው ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነትን መካድ፣ አዲስ ታሪክ መጻፍ፣ ባዕድ ነን ማለት፣ የሕዝብ መቀራረብን ማውገዝ፣ ጥላቻን ማናፈስ፣ የልዩነት ቅስቀሳን ማጧጧፍ፣ መገንጠል ወይ ሞት ብሎ መፈጠም....እነዚህ ሁሉ የሕዝብ ሳይሆኑ በግንጠላው እንጠቀማለን፣ የራሳችንን ብቸኛ ሀገር መሥርተን ገዢ እንሆናለን ወዘተ ብለው የሚመኙ ምርጦች ወይም ውሱን ክፍሎች አቋሞች ናቸው፡፡ የብሔርተኛነትን ኤኮኖሚያዊ መሠ ረቱንም መዘንጋት የለብንም፡፡...ስለዚህም ለሀገር አንድነት የሚካሄደው ትግል ከግቡ እንዲደርስ ከተፈለገ ከሁለት ዕንፎች--የአንድ ብሔርተኛነት ሁለት ገፅታዎች--መራቅ የግድ ነው፡፡ በአንድ ዕንፍ የሚታየው ጎጂ አቅዋም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ክዶ በመብት ሽፋን ግንጠላን እያራገበ በክልል፣ በአሶሳ፣ በአረካ፣ በአርባጉጉ፣ በአሰቦት፣ በበደኖ ወዘተ... እልቂቶች የሚገለፀው ነው፡፡ ይህ በተለይ ትግራይ-ትግሪኚው ገዢ ክፍል፣ በአጋሮቹና በመሰሎቹ እየተራገበ ያለው የጥላቻና የክፍፍል እሳት ታሪክን እየካደ፣ የርስ በርስ ግጭትን እያስፋፋ፣የአንድነትን ሥረ መሠረት እየነቃቀለ ሕዝብን በብሔረሰብና በክልል ደረጃ በልቶና ሸንሽኖ፣ አሽመድምዶ ለጥፋት የሚዳርግ ነው፡፡ ይህ ፀረ ኢትዮጵያ ዕንፈኛ አቅዋም መገንጠል ወይ ሞት በሚለው መፈክሩና ተግባሩ ይገለጣል፡፡ የሕዝብን ማንነትና የጋራ ታሪክ ይሰርዛል፡፡ በኢትዮጵያዊነት ላይ ሳይታክት ይዘምታል፡፡ ዘረኛነትን እንደ ፀጋ ተላብሶ ለዴሞክራሲ አፍአዊ ግብርን እየከፈለ ክፍፍልን ያነግሳል፡፡ ሌላኛው ዕንፋዊ አቅዋም ደግሞ ራሱን በአንድነት አባወራነት ሰይሞ በጥቅል መፈክር ተጨባጭ ሁኔታን እየካደ በህሊናውም በጆሮውም ላይ የተኛ ነው፡፡ ተበደልን ባዮችን፣ ተጨቆንን ባዮችን አያዳምጥም፡፡ ሁሉ የሚያውቀውን እውነታ ይክዳል፡፡ ያልተከበረን መብት እንደተከበረ ያቀርባል፡፡ የብዙኃኑን የብሶት ድምፅ ማዳመጥ እየተሳነውም የአፄውን ዘመን ይመኛል፡፡ ለሕዝብ ሉዓላዊነት ከአፍአዊ ደረጃ ባሻገር ሚዛን ስለማይሰጥም በኃይል ይተማመናል፡፡ በጨቋኙ ሥርዓት ላይ በመዝመት ፈንታ ለጭቆና መፍትሄ ሲሹ መብት ይከበር ያሉትን በምሬት ያወግዛል፡፡እንደ ወያኔ ሁሉ ይህኛውም ዕንፍ የአንድነት መሰረቱ የሕዝቦች መብት መከበር መሆኑን በገቢር ይፃረራል፡፡

ሁለቱም ዕንፎች ከአንድ የብሔረተኝነት ምንጭ የተቀዱና ብሔረሰቦችን- አቀፍ ለሆነች አንዲት ሀገር ጠር የሆኑ ናቸው፡፡ የሕዝብን ሳይሆን የራሳቸውን ጠባብ ጥቅም በአደናጋሪ ዲስኩር ሸፍነው ስሜት በመኮርኮር አለባብሰው በዋናነትና በተቀዳሚነት የሚሰየሙ ናቸው፡፡ለሀገር አንድነት የሚታገሉ ለወያኔ ከፋፋይ ፖለቲካ ተፃራሪ መሆን እንዳለባቸው ሁሉ ወያኔን እቃወማለሁ እያሉ የወያኔ ግልባጭ በመሆን የሕዝብ አንድነትን ከሚያጠፉ ዕንፈኛ አቅዋም ርቀው-ተጣልተው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡"

ኢሕአፓ የዕንፈኞቹን ጉዳትና አደጋ ከማጋለጥ ባሻገር ለተከሰቱ ችግሮች ተጨባጭ መፍትሄን ከማቅረብ አንፃር በመጋቢት 1981 "የኤርትራ ጥያቄ" በሚለው ፅሁፉ ለምሳሌ የችግሩን ሂደት ከመረመረመና በየጊዜውም ኢሕአፓ በጥያቄው ላይ የነበረውን አቅዋምም ከእንማጠየቂያው ካቀረበ በኋላ ለኤርትራ የፌዴሬሽን መፍትሔን ያዋጣል ብሎ የበኩሉን መፍትሄ ሀሳብ አቅርቦ ነበር፡፡ ይህንን አቅዋም ሳይውል ሳያድር በትምክህተኛነት ወያኔም ሻዕቢያም ያወገዙትና በተቃራኒም መገንጠልን የገፉ ቢሆንም ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሳይፈጠር ይህም ጥያቄ ሆነ ሌሎች በሚገባ ሊፈቱ አይችሉም ብሎት የነበረውን እነሆ ዛሬም ባለው ሁኔታ ሐቅነቱን እያየነው ነው፡፡ መገንጠል ለኤርትራ ሕዝብ የሚጠቅመው አማራጭ አይሆንም ያለው ኢሕአፓ ለምን ይህንን እንዳለም ሲያስረዳ የሚከተለውን ፅፎ ነበር፣

" የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕዝብን በደል ሊረዳ ቢችልም፣ መገንጠልን መደገፍ አይዋጥለትም፡፡...አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገር አንድነት ያለው ስሜት ጠንካራና ቋሚ በመሆኑ "የሀገር አንድነት" የሚለው መፈክር የሚሠራና የሚያገለግል ነው፡፡...ባጭር ቃል የኤርትራን ጥያቄ በመገንጠል ደረጃ ሳይሆን ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጋር

በተሳሰረና ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድል ጋር በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በተቆራኘ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረጉ ለዘለቄታ ሰላም፣ ለዘለቄታ የሕዝብ ጥቅም ለጋራ ብልፅግና አስፈላጊና ገሀድ የሆነ ምርጫ ሆኗል::"

ይህን ብሎና አብራርቶ ኢሕአፓ ያቀረበው የፌዴራል መፍትሔ ሰሚ ተቀባይ ሳያገኝ ቀርቶበጠባቦቹ ጎዳና የተፈጸመው ሌላው ምርጫቸው እነሆ ዛሬ ሕዝብን እያጫረሱና ያምርብናል ያሉትንም ከትቢያ ደባልቀና ከድኽነትም ላይ ጥሎ እያሰቃየ እንደሆነ ለማየት በቅተናል:: ተገነጠልን-አስገነጠልን ካሉም በኋላ ፊት ያክቸለቸሉትን የፌዴራል መፍትሔም "ለሁለቱ ሀገሮች" ይጠቅማል በሚል ለማቀራረብ ሲቃጡም ሰምተናቸዋል:: የፌዴራል መፍትሔን ኢሕአፓ ሲያቀርብ በደፈናው ሳይሆን በሚከተለው መንፈስ እንደነበር ከላይ የተጠቀሰው ጽሑፍ በወቅቱ አብራርቶታል፣

" ኢሕአፓ ይህን ፌዴራላዊ መፍትሔ ለኤርትራው ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ይህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በኢትዮጵያ በአጠቃላይ--ኤርትራንም ጨምሮ--በፖለቲካው መስክ ልዩ ልዩ ፓርቲዎችን ያቀፈ የፖለቲካ ሥርዓት /መልታይ ፓርቲ ፖለቲካል ሲስተም/ ሊሰፍን ሲችልና የአንድ ፓርቲ ወይም ቡድን አምባገነንነት ሊከሰት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው ብሎ ስለሚያምን ከዚህ ውጪ ባለ ሁኔታ፣ ይህን ባላሟላ አገባብ ፌዴራላዊም ሆነ ሌላ ግንኙነት፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ዕድገት ሊያመጣ አይችልም ይላል:: ስለሆነም ከዚህ አንፃርም ከሚያቀርበው መፍትሔ ጋር ይህንኑ ጉዳይ በግልፅ አያይዞ ያስቀምጣል፣ ያብራራል፣ ይቀሰቅሳል::"

በዚህ ሳያበቃም ኢሕአፓ የሬፈሬንደምን ሂደት በተመለከተም ተገቢውን ማብራሪያ የሰጠ እንደነበር ማስታወሱ ኋላ ከተከሰተው-ከተገባደደው ጋር ለማነፃፃሩም ይጠቅማል::

" የኤርትራ ግንባሮች/በተለይምሕግሓኤ/ እንዲሁም እንደ ሕወሓት ያሉ ግንባሮች ሬፈሬንደምን መቀበል የብሔሮችን መብት ለመቀበል እንደ ብቸኛው ማረጋገጫ/መመዘኛ አድርገው ይወስዱታል::ሆኖም ሬፈሬንደም የሕዝብን ምርጫ በማሳየት ረገድ ትርጉም የሚኖረው በግብር የሚውልበትም መደላድል ሲኖረው ሰለሆነ፣ እነሱ የሚሉት የሬፈሬንደም ትርጓሜናኢሕአፓ የሚለው ጉልህ ልዩነት አለው::

እነሱ ሬፈሬንደም ሲሉ በደርግና በነሱ መካከል ሕዝቡ ምርጫ ያድርግ ማለታቸው ሲሆን የሚንደረደሩትም ሕዝቡ ከደርግ ይልቅ እኛን ይመርጣል ከሚል እምነት በመነሳት ነው:: ኢሕአፓ በመሠረቱ ሬፈሬንደምን እንደ አንድ የሕዝብ ምርጫ መከሰቻ መንገድ አድርጎ ሲቀበለው የሬፈሬንደም ጉዳይ በኤርትራም በቀረውም የኢትዮጵያ ክፍል መኖር ከሚያስፈልገው ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ጋር አጣምሮ በማየት ነው:: ኢሕአፓ ሬፈሬንደም ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ዴሞክራሲን በተቀበለና በፈቀደ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን መራጩ ሕዝብ ከፋሺስታዊ መንግስትም ሆነ ከማንኛውም ሌላ ኃይልም ሆነ ኃይሎች ግፊት ነፃ ሆኖ ሳይሸማቀቅ፣ በትክክል የሚሰማውን ስሜትና ፍላጎት ሊገልፅበት በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ሳይገኝ ሬፈሬንደም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ይላል:: ተፈላጊውን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመፍጠር ደግሞ በኤርትራና በተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙት ዴሞክራሲያዊን ኃይላት ትግላቸውን አደጋግፈው በየአቅጣጫቸው ለዴሞክራሲ መሠረት መጣልና የሕዝብ እምነት፣ ፍላጎት፣ ምኞት ሳይታፈን እንዲንፀባረቅ፣ ነፃ የፖለቲካ አየር እንዲነፍስ ሠፊ መድረክ እንዲዘረጋ ማድረግ ታሪካዊ የሆነ የጋራ ኃላፊነታቸው መሆኑን መቀበል ይጠበቅባቸዋል::" ብለን ነበር::

ወያኔና መሰሎቹ ይህን ግዴታ ሊቀበሉ ቀርቶ ይህንኑ ያሳሰባቸውን ኢሕአፓን አውግዘው በተደጋጋሚ በጦር እንደዘመቱበትና ለዘመናት ይዘልቅልናል ያሉትን ወዳጅነት መከሰቻ የሆነውን የግንጠላ ሂደት በፈለጉት መንገድ እንደ አከናወኑ አይተናል:: የአንድነትን ጥሪ

ሊቀበሉ ቀርቶ ሊያስቡበት እንኳን አልፈለጉም፡፡ ቀና መፍትሔውም ከትቢያ ተወርውሮ እነሆ መገንጠሉም ተጠናቆ ውሎ አድሮ ኢሕአፓ እንዳለው ሰላምም ሌላውም ሁሉም ሁሉም የውህ ሽታ ሆኖ እርስ በርስ በመናቆርና ሕዝብንም በማጫረስ ላይ ይገኛሉ፡፡ ተሳስተን ነበርን ብለው ያሰላስላሉ ብለን መገመት አንችልም፡፡

ወያኔ የተባለው ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን በባዕዳን ተደግፎ በመላዪቱ ኢትዮጵያ ላይ ባለ ሥልጣን ከሆነብን ጀምሮ ደግሞ በሀገራችን አንድነት ላይ በነጋና በጠባ የፈፀመውንና እየፈፀመ ያለውን ጥቃት የምናውቀው ነው፡፡ ሕዝብን በብሔረሰብ ደረጃ ውልቅልቁን አውጥቶ ከፋፍሏል፣ ልዩነትን በአሉታዊ ገጽታዎቹ ወጥሮና በአንድነት ላይ ፈንጂ አድርጎ ተጠቅሞበታል፣ መገንጠልን በመርህ ደረጃ በሕገ መንግሥቱ አስገብቷል፥ ቋንቋን ለመለያያ አውሎታል፣ መብትን በማስከበር ሽፋን በኢትዮጵያዊነት ላይ ዘምቷል፡፡ የወያኔ ስርዓት በሀገርና በሕዝብ ላይ በሁሉም መስክ ያደረሰውና እያደረሰ ያለውን በተመለከተ ተደጋግሞ የተገለፀና በሚገባም የሚታወቅ በመሆኑ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በወያኔ አጥፊነት ላይ ሳይሆን ለሀገር አንድነት ምን መደረግ አለበት በሚለው ላይ ነው ያተኮርነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ መተኮር እንዳለበት መቀበሉ ይመረጣል፡፡ የኤርትራም ግንባሮች ለጊዜወም ቢሆን የፈለጉት ሌላ ሀገር መሆንን በተመለከተ አዲስአበባ ባስቀመጡት ሎሌአቸው ትብብር የተሳካላቸው ቢመስልም ባለፉት ዓመታት ያየነው ሐቅ ግልፅ የሚያደርግልን ከሕዝብ መብት ጥቅምና እንዲሁም ብልፅግና አኳያ የተወሰደው የመገንጠል አማራጭ አጥጋቢ ውጤትን ጭራሽ እንዳላስገኘ ነው፡፡ ይህም ጉዳዩን እንደገና በጥሞናና ከስሜታዊነት በራቀ መንፈስ እንድናየው ያስገድደናል፡፡ የኤርትራ ሁለገብ ችግርና የተካሄደውም አጥፊ ጦርነት ቢሆን በመሠረቱ ነፃነት ከተባለው ክስተት ጋር የተቆራኘ መሆኑ ግልፅ ሆኗል፡፡ ያለንበት ዘመን ደግሞ የዓለም ሕዝቦች ለደህንነታቸውና ለዕድገታቸው ለመታገል ማበር መተባበርን እየመረጡ የመጡበት በመሆኑ የራስ የተለየን ባንዲራን ለማውለብለብ ከሚብከነከን ፍላጎት ባሻገር የሕዝብን የጋራ ጥቅም አስቀድሞ የአንድነትና ኅብረትን ጎዳና መምረጡ ከዘላቂው የሕዝብ ጥቅም አንፃር የግድ ነው፡፡ በአውሮጳ ደረጃና አልፎም በአፍሪካም ቢሆን ተመሳሳይ የአንድነት፣የውህደት ሙከራ አለ ፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ያሉትን በድህነት የተቆራመዱ ሀገሮች ሁሉ ስናይ ደግሞ ይህ ተለያይቶ ኑሮ ምንኛ ጎጂ ቅዠት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በመሆኑም በሂደቱም በገሀድ ልናይ እንደቻልነው የኤርትራ ዕጣ ከቀሪው ኢትዮጵያ ዕጣ ሊለይ የቻለበትና የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ አለ ከተባለም ዛሬ የሚታየው ድህነትናግጭት ለዘመናት እንዲቀጥል መፈለግ ይሆናል፡፡ ከዚህ ሌላ ኢሕአፓ በአሁኑ ወቅት ይህ ትስስር ያ ትስስር ማለት ባይገደድም የመገንጠሉ እውነታ ያመጣውን ቁርሾና መዘዝ ሆነ የባህር በር ጉዳይን በተመለከተም ቢሆን፣የአፋርና የሌሎችንም የአንድነት ፍላጎት ለማሟላትሆነ በጋራ ከባዱን የእድገት ጥረት ለመጋፈጥ ከማበርና በዴሞክራሲያዊ መሰረት በአንድ ለመኖር እንደገና በትዕግስትና በስልት ከመሞከር ሌላ የተሻለ አማራጭ የለም ይላል፡፡ ይህንኑም አማራጭ በጊዜው ለሌሎቹም የአካባቢው ሕዝቦች "የሚያዋጣውና ለሁሉም የሚበጀው ይህኛው አማራጭ ነው " ብሎ ማቅረብም ያስፈልጋል ሲል ኢሕአፓ ያምናል፡

የወያኔን የክልል ፖለቲካ በተመለከተ ደግሞ በብሔረሰብ ደረጃ ሕዝብን ማካለሉ ለክፍፍልና ለግጭት እንዲሁም ለየክልሉ ተለጣፊዎች ቡድናዊ ጥቅም ማካበቺያነት እንጂ ለሕዝቡ መብት መከበርና ለአንድነት መጠናከር የፈየደው ቅንጣትም ነገር የለም፡፡ የክልል ሕዝብ መብቱን አላገኘም፣ ራሱን ለማስተዳደርም አልቻለም፡፡ የየክልሉም ሆነ የሀገሪቷም የኤኮኖሚ ሁለገብ ዕድገት ላይ ይህ ዓይነቱ አከፋፈል ጋሬጣ ሆኗል፡፡ የወያኔ የብሔረሰብ ፌደራላዊ አስተዳደር ከፌዴሬሽን ፅንሰ ሀሳብና ክስተት ጋር የተጋጨ ከመሆኑ ሌላ ሕዝብን በዘፈቀደ በብሔረሰብ ከልሎ ማራራቅና በአሉታዊ ፉክክር መክተት የአንድነትና የዕድገት ጠንቅ መሆኑም ታይቷል፡፡

ኢሕአፓ በፕሮግራሙ የፌዴራላዊ ቅርፅን የደገፈው ከወያኔ በተቃረነና በተለየ ቢሆንም ዋናው ቁምነገር ሕዝብን አለመከፋፋሉና የማካለሉ አላማም የሕዝብን ፍላጎትና ኤኮኖሚያዊ ግብን በቅድሚያ ያስቀመጠ መሆኑ ላይ ቢሆን የሚመረጥ ነው፡፡ አንድ ቋንቋ የሚናገር

ሕዝብ በተለይ ክልል ተከማችቶና በዋና መልኩ ብዙሃኑ ሆኖ በሚገኝበት ይህንኑ ለኤኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እስከጠቀመ ድረስ ልንጠቀምበት የምንችል ቢሆንም የወደፊቷ ኢትዮጵያ አስተዳደራዊ መልኳ የጠበቀ ማዕከላዊ ሥልጣንን በሕዝብ ወሳኝነትና ራስ ማስተዳደር መብት የሚተካና በቅድሚያ በኤኮኖሚ ዕድገት አመቺነት ዙሪያ የተዋቀረ ቅርፅ ቢሆን የተሻለ ይሆናል። የኢትዮጰያን ሕዝብ አንድነት የሚያዳብርና የሚያጠናክር ፖሊሲና ቅርፅ መወሰን ይኖርበታል እንጂ የተጎዳውን ሕዝብ ይበልጥ የሚከፋፍል የሚነጣጥልና ብሎም ለባሰ መከራ የሚያጋልጥ መሆን የለበትም። ይህን በተመለከተ ሕዝቡና ድርጅቶቹ ሁሉ በቀና መንፈስ ያለፉትን የአስተዳደር ቅርፆች መርምረውና ተወያይተው ፕሮግራማቸውንም አጣጥመው መፍትሔ የሚያገኙለት መሆኑም አያጠራጥርም። ለሁሉም መሠረቱ ግን የሕዝብ እኩልነት እውን የሆነባት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ላይ የተገነባች የጋራ ሀገር እንድትኖረን በጋራ መነሳትና መታገሉ ላይ ነው። የሕዝቡ ቋንቋዎች፣ ባህሎች ወዘተ... ሁሉ ተከብረው ለአንድነቱ መሠረት የሚሆኑብትን መንገድም ማመቻቸት የሚቻለው በዚሁ መንገድ ነው።

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ለአንዴም ለሁሌም የመገንጠልን አማራጭነት ውድቅ አድርገው የዴሞክራሲያዊ አንድነትን አማራጭ-የለሽነት እንዲቀበሉና ለዚህም ተባብረውእንዲታገሉ ጥሪ ያደርጋል። ኢትዮጵያዊነት ደግሞ የሁሉም ትግልና መስዋዕትነት ውጤት በመሆኑ ማንም ቢሆን ማን ይህንን መለያውን ሊቀማ ካለመቻሉ ሌላ ሊጠራጠረውም የሚገባ ጉዳይ አለመሆኑም ሊታመንበት ይገባል። የብሔረሰቦች ወግ፣ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋዎች ተከብረው ለሀገራዊ አንድነታችን ጠቃሚ የሆኑ ቅርሶቻችችንና-እሴታችን መሆናቸውም ታምኖበት ሁላችንንም በእኩልነት ያቀፈች ታላቅ ሀገርን፣የሁሉም ሕዝብዋ የጋራ የሆነችሀገርን በጋራ ልናጠናክር እንችላለን ብሎ ኢሕአፓ ያምናል። ለዚህም ልክ እንደ በፊቱ ይህንን ቅዱስ ዓላማችንን ከሚፃረሩ ፅንፎች መራቅና በተከሰቱበትም መታገል ይኖርብናል። ለእኩልነትና ለመብት መከበር መቆም ተገቢና ፍትሀዊ ነው። ለሀገራችን ለኢትዮጵያ በጋራ መታገልና ዜግነታችንንም ማስረገጥ ደግሞ ግዳጃችን ነው። በዚህ መልክ ሲታይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት በዴሞክራሲ ለም ማሳ ላይ ጸድቆ እውን እንዲሆን በመታገል የወያኔን ዘረኛና ከፋፈይ አገዛዝ ማስወገድ የሁላችንም ተቀዳሚና ዋና ተልዕኮ ሊሆን ይገባዋል ሲል ኢሕአፓ ያሳስባል።

ስለዚህም ኢሕአፓ ሁሉም ድርጅቶች (በብሔረሰብ ደረጃ ተደራጁትም ሆኑ በኅብረብሔርነት የተደራጁት) ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን በጋራ እንዲታገሉ ዳግም ጥሪ እያደረገ ለቀጣይ ጥረቶችም ዝግጁነቱን ያረጋግጣል። በኤርትራ ላሉ ወገኖቻችን ደግሞ ያለፉትን ዓመታት በሚገባ አጢነውና ለሐቅና ለታሪክ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድ ሰላምና እድገት ማስገኘትን ቅድሚያ ቦታ ሰጥተው በአዲስ መንፈስና መንገድ የአንድነትን ምርጫ በድፍረት እንዲወስዱ፣ የዴሞክራሲያዊ ትስስርን መንገድን እንዲመርጡ ጥሪ ያደርግላቸዋል።የኢትዮጵያ ሕዝብ በበኩሉ ለጠባቦችና ከፋፋዮች ሳያመች፣ ለትምክህተኞች ጆሮ ሳይሰጥ ታሪካዊ አንድነቱን በዴሞክራሲ አድሶ ውድ ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን እንዲነሳ ኢሕአፓ ይጠራዋል።
ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለሀገር አንድነት ይዋደቅ!
መገንጠልና መከፋፈልን ማቀንቀን ፀያፍ ይሁን!
ሀገራችን የሁላችንም የጋራችን ናትና በጋራ ትግል ህልውናዋን እናስከብር!!
የሀገር አንድነት መሰረቱ የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብትና እኩልነት ነው!!
ፀረ ሕዝቡን የወያኔ አገዛዝ በህብረት ትግል እናስወግድ!!